ውበየወ/መ/ቁጥር 161635

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ግንቦት 23 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ 1 ኛ ተመስገን ኢሳያስ ሱንዳዶ - ከማረሚያ ቤት ቀረበ

2 ኛ ደስታ ያዕቆብ ጋንቤላ - ከማረሚያ ቤት ቀርቧል

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ታህሳስ 07 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ ተከሳሾች በበ 1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 32(1)(ሀ) እና 669(3)(ለ) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለማግኘት አስበው ጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት በሚሆንበት ሰዓት ኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 08/09 ልዮ ቦታው 18 ማዞሪያ ታክሲ ተራ አካባቢ ቁሞ የነበረ ንብረትነቱ የግል ተበዳይ ግርማ በክረፅዮን የሆነ ሠሌዳ ቁጥሩ 1- 17816 አ/አ ሚኒባስ ታክሲ መኪና በተመሳሳይ ቁልፍ በመክፈት በአንደኛ ተከሳሽ አሽከርካሪነት ወደ ጉራጌ ዞን ቸሀ ወረዳ እንድብር ከተማ መኪናውን በመውሰዳቸውና ከአካሉ ላይ 1 ኛ) ሶስት ጎማ ከነቸርኪው፤ 2 ኛ) የመኪናው ባትሪ፤ 3 ኛ) ቴፕ፤ 4 ኛ) አንድ እስፖኪዮ ጎድሎ የተገኘ በመሆኑ በግብረአበርነት በፈፀሙት ከባድ የስርቆት ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሾች ደርሷቸውና ተነቦላቸው ከተረዱት በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ፤ ድርጊቱን አልፈፀምንም፤ ጥፋተኞች አይደለንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ዐ/ሕግ ምስክሮቹን አቅርቦ ካሰማ በኋላ ዐ/ሕግ እንደ ክስ አቀራረቡ ስላስረዳ ተከሳሾች በተከሰሱበት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 669(3)(ለ) ስር እንዲከላከሉ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዘዋል።

አንደኛ ተከሳሽ የመከላከያ ማስረጃ የለኝም በማለቱ አላሰማም። ሁለተኛ ተከሳሽ ግን እከላከላለሁ ብሎ አንድ የመከላከያ ምስክር አቅርቦ ያሰማ ሲሆን በመከላከያ ጭብጥነትም ያስመዘገበው ከጥቅምት 24 ቀን 2002 እስከ ጥቅምት 28 ቀን 2002 ዓ.ም ድረስ የወባ በሽታ አሞኝ ቤቴ ተኝቼ ነበር፤ እህትና ወንድሜም ነበሩ፤ በጥቅምት 26 ቀን 2002 ዓ.ም የአሁን

የመከላከያ ምስክሬ መጥቶ ጠይቆኛል በማለት አስመዝግቧል። የመከላከያ ምስክሩም በእምነቱ መሰረት መኃላ ፈፅሞ የመሰከረ ሲሆን ቃሉም ከመዝገቡ ጋር ተያይዟል።

ፍ/ቤቱም ሁለተኛ ተከሳሽ ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ አስተባብሏል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ ተከሳሽ አምስት ቀን ያህል ታሞ ሲተኛ ሐኪም ቤት አይሄድም ስለማይባል፤ ቢታመም ኖሮ የህክምና ማስረጃ ያቀርብ ነበር። በመቀጠል ሁለተኛ ተከሳሽ በወቅቱ ከወንድሜ እና እህቱ ጋር ቤት ውስጥ እያለሁ ነው የመከላከያ ምስክሩ የመጣው በማለት ጭብጡን ያስያዘ ሲሆን፤ ነገር ግን ምስክሩ ቀርቦ ሲያስረዳ ተከሳሽ በወቅቱ ብቻውን ነው የነበረው፤ የሚኖረውም ብቻውን ነው በማለት ነው ቃሉን የሰጠው። በሦስተኛ ደረጃ ሁለተኛ ተከሳሽ በፖሊስ ጣቢያ ቀርቦ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 27(2) መሰረት ቃሉን የሰጠ ሲሆን በዚሁ ላይም የወንጀል ድርጊቱን የፈፀመ መሆኑን ነው የገለፀው፤ ነገር ግን አሁን በምንም አይነት የመከላከያ ማሰረጃ ይህን አላስተባበለውም። ስለሆነም ሁለተኛ ተከሳሽ ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ የቀረበበት ክስና ማስረጃ ያላስተባበለ በመሆኑ፤ አንደኛ ተከሳሽ ቀድሞውን ቢሆን የመከላከያ ማስረጃ የለኝም ብሎ ስለገለፀ፤ ሁለቱም ተከሳሾች በወንጀል ሕግ አንቀፅ 669(3)(ለ) ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ ተከሳሾች ድርጊቱን የፈፀሙት በጋራ ስለሆነ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1(መ) መሰረት ቅጣቱ ከብዶ እንዲወሰን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሾች</u>፡ አንደኛ ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 21 ዓመት፤ ሥራዬ የመኪና ረዳት ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ 4 ኛ ክፍል ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ ድርጊቱን የፈፀምኩት እናቴ ታማ ለማሳከሚያ ገንዘብ አስፈልጓት ስራ ስላልነበረኝ ነው በማለት አመልክቷል።

ሁለተኛ ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 18 ዓመት ነው፤ የትምህርት ደረጃዬ 5 ኛ ክፍል ነው፤ ትዳርና ልጅ የለኝም፤ የምኖረው ከወንድሞቼ ጋር ነው በማለት አመልክቷል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ቅጣቱን በወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2000 መሰረት ለመወሰን እንዲቻል ዐ/ሕግ በክሱ ዝርዝር ውስጥ የገለፀው የጉበረት ጥቅም

ጉዳት መጠኑን በማስረጃ አስደግፎ እንዲያቀርብ ታዟል።

2 ኛ. ቅጣቱን ለመወሰን ለሰኔ 03 ቀን 2002 ዓ.ም ጠዋት 3፡00 ሰዓት ተቀጠረ።

የወ/መ/ቁጥር 161635

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ግንቦት 30 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ 1 ኛ አቶ ተመስገን ኢሳያስ - ከማ/ቤት ቀረበ

2 ኛ አቶ ደስታ ያዕቆብ - ከማረሚያ ቤት ቀረበ

መዝገቡ ለዛሬ የተቀጠረው ዐ/ሕግ በተከሳሾች የወንጀል ድርጊት ምክንያት የደረሰውን የንብረት ጥቅም ጉዳት ሲያቀርብ ቅጣቱን ለመወሰን ሲሆን በዚሁ መሰረትም ዐ/ሕግ ግንቦት 27 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ደብዳቤ በወቅቱ ተከሳሾች የሰረቁት ንብረት ግምት ብር 150,000.00(አንድ መቶ ሃምሳ ሺህ ብር) ነው በማለት አቅርቧል፤ ተከሳሾችም ይሄው

ደርሷቸው ተቃራኒ ማስተባበያ ማስረጃ አላቀረቡም። ፍ/ቤቱም መዝገቡን መርምሮ የሚከተለው የቅጣት ውሳኔ ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ሊያሳካ እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ኩበደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

ሁለቱም ተከሳሾች ጥፋተኛ የተባሉበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 669(3) (ለ) ደረጃ የወጣለት ወንጀል በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና አባሪዎቹ መሰረት የተመለከተው ደረጃ 7 ሲሆን ተጓዳኝ መነሻ እርከኑም 21 ነው። ስለሆነም የዚህ እርከን መነሻ ፈቃደ ስልጥን/range/ ከአምስት ዓመት እስከ ስድስት ዓመት እስራት የሚያስቀጣ ነው ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም ፍ/ቤቱ የወሰነው መነሻ ቅጣት አምስት ዓመት ከስድስት ወር ፅኑ እስራት ነው።

በዚህም መሰረት የግራቀኙን የቅጣት አስተያየት አመዛዝኖ ቅጣት ለመወሰን ዐ/ሕግ በተጠየቀው መሰረት በወንጀል ሕግ አንቀፅ 84(1) (መ) መሰረት ተከሳሾች የወንጀል ድርጊቱን የፈፀሙት በጋራ ስለሆነ ቅጣቱ እንዲከብድ በማለት የጠየቀ ሲሆን ይህም ማስረጃ የሚቀርብበት ሳይሆን ከክስ አቀራረቡ እና ከጠቅላላው የድርጊቱ አፈፃፀም ለመገንዘብ የሚቻል በመሆኑ ፍ/ቤቱም ጉዳዩን እንደመረመረው የቀረበው አንድ የቅጣት ማክበጃ ምክንያት ስለሆነ በመመሪያው አንቀፅ 14(4) መሰረት ከመነሻው ቅጣት ከአምስት ዓመት ከስድስት ወር ከሚያርፍበት ከእርከን 21 በአንድ በመጨመር እርከን 22 ላይ ይወሰናል።

ተከሳሾችም በበኩላቸው የቅጣት ማቅለያ አስተያየት ተጠይቀው በወንጀል ሕግ አንቀፅ 82 መሰረት በተመለከቱት ሁኔታ አላቀረቡም። በወንጀል ሕግ አንቀፅ 86 መሰረት ደግሞ የትምህርት ደረጃቸው ዝቅተኛ መሆንን፤ ቤተሰብ እንደሚረዱና ለዚሁ ለቤተሰብ እርዳታ ብለው ወንጀሉን የፈፀሙ መሆኑን ቢገልፁም፤ በማስረጃ ያልተደገፉ ስለሆኑ ፍ/ቤቱ የቅጣት አስተያየቶቹን አልተቀበላቸውም።

ስለሆም በማክበጃ ምክንያቱ መሰረት ከፍ ብሎ በተወሰነው እርከን መሰረት የተቀመጠው ፈቃደ ስልጣን/range/ ከአምስት ዓመት ከስድስት ወር እስከ ስድስት ዓመት ከሰባት ወር ፅኑ እስራት የሚያስቀጣ ሲሆን ፍ/ቤቱም የወንጀል ክብደቱንና የተከሳሾችን የግል ሁኔታ አመዛዝኖ እያንዳንዳቸው በስድስት ዓመት/ 6 ዓመት/ ፅኑ እስራት እንዲቀጡ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. የአዲስ አበባ ማረሚያ ቤት በተከሳሾች ላይ የተወሰነው የእስራት ቅጣት
ቀደም ሲል በሌላ የወንጀል ድርጊት የተቀጡ ከሆነ ከተወሰነው ጋር
በማጣመር የእስራት ቅጣቱን እንዲያስፈፅም ታዟል።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. በዚህ መዝገብ የተሰጠ የዋስትና ግዴታ ካለ ቀሪ ሆኗል።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።